https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፮
አዲስ አበባ ኅዳር ፬ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.56
ADDIS ABABA November 13th, 2018

<u>ማውጫ</u>

ደንብ ቁጥር ፬፻፳፱/፪ሺ፲፩

የሊድ ቀለምን ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮችምክር ቤት ደንብ……………………………………………ገጽ፲ሺ፬፻፴

**CONTENT**

Regulation No.429/2018

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO CONTROL LEAD IN PAINT…......................page 10430

ደንብ ቁጥር ፬፻፳፱/፪ሺ፲፩

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፱/፪ሺ፲፩

## የሊድ ቀለምን ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ፱፻፲፮/፪ሺ፯ አንቀጽ ፭ እና በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፫፻/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፳ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሊድ ቀለምን መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፱/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩ በአዋጁ አንቀፅ ፪ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፪/ "ቀለም" ማለት ቫርኒሽን፣ ላኳየርስ፣ ስቴይንስ፣ ኤናሜልስ፣ ግላዝስ፣ፕሪመርስ ወይም ማንኛውም

Regulation No. 429/2018

Council of Ministers Regulation No 429/2018

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO CONTROL LEAD IN PAINT

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 and Article 20 of the Environmental Pollution Control Proclamation No. 300/ 2002.

## SECTION ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Lead in Paint Control Council of Ministers Regulation No. 429/2018".

### 2. Definition

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ Definitions provided for under Article 2 of the proclamation shall be applicable to this Regulation.

2/ "paint" means varnishes, lacquers, stains, enamels, glazes, primers or coatings used for

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

https://chilot.me

ለቅብ አገልግሎት የሚውል ሲሆን እና በዋናነት የሬዚንስ፣ ፒግመንት፣ ፊለርስ፣ ሶልቨንትስ እና ሌሎች አድቲቨስ ድብልቅ/ ቅይጥ ነው፤

፫/ “የሊድ ቀለም” ማለት አንድና ከአንድ በላይ የሊድ ውህድ የተጨመረበት ቀለም ሲሆን በሊድ ካርቦኔት፣ ሊድ ክሮሜት፣ ሊድ ክሮሜት ኦክሳይድ፣ ሊድ ክሮሜት ሞሊብዴት ቀይ ሰልፌት፣ ቢጫ ሊድ ሰለፈሮክሮሜት፣ ሊድ ፪ ኤታይልሂክሶኔት፣ ሊድ ሞሊብዴት፣ ሊድ ናፍቴኔት፣ ሊድ ናይትሬት፣ ሊድ ሞኖኦክሳይድ፣ ሊድ ኦክሳይድ፣ ሊድ ኦክታኔት፣ ሊድ ፐርኦክሳይድ፣ ሊድ ሰልፌት እና ትራይ ሊድ ባይካርቦኔት ዳይሀይድሮኦክሳይድ ይጨምራል፤

፬/ “ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች” ማለት የሕፃናት አሻንጉሊቶች፣ የቤት ውስጥና የውጪ የሕፃናት የመጫወቻ ዕቃዎች፣ የሕፃናት መጽሐፍት፣ የስዕል መሣሪያዎች፣ የቤት ቁሳቁሶችና ሌሎች ሊድ ያለው ቀለምን የሚጠቀሙ ምርቶችን ይጨምራል፤

፭/ "የተስማሚነት ምዘና የምስክር ወረቀት" ማለት ሊድ ያለው ቀለም ምርት በዚህ ደንብ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የሊድ መጠን መያዙን በማረጋገጥ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

፮/ “መለያ” ማለት በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፈ፣ የታተመ ወይም በምስል የተቀረፀና በቀለም ቀጥተኛ መያዣና በቀጥተኛ መያዣዎቹ ውጫዊ መያዣ ወይም መጠቅለያ ላይ የተደረገ ወይም ከነዚሁ ጋር የተያያዘ አጠቃላይ የሊድ መጠንን የሚገልፅ መግለጫ ነው፤

፯/ “አጠቃላይ የሊድ መጠን” ማለት የምርቱ ወይም የደረቀው ቀለም አጠቃላይ ሊተን የማይችል ክብደት በመቶኛ መጠን ነው፤

፰/ “አግባብነት ያለው አካል” ማለት በዚህ ደንብ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት በቀለም ውስጥ የሊድ መጠንን ለመቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው መንግሥታዊ አካል ነው፤

፱/ “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደየቅደም ተከተላቸው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፩/ በወንድ ጾታ የተገለፀው ድንጋጌ ሴትንም ያካትታል።

any purposes; and is typically a mixture of resins, pigments, fillers, solvents and other additives;

3/ “Lead paint” means paint to which one or more compounds typically added to paint and includes lead carbonate, lead chromate, lead chromate oxide, lead chromate molybdate sulpahte red, lead sulphrochromate yellow, lead 2-ethylhexnoate, lead molybdate, lead naphthenate, lead nitrate, lead monoxide, lead oxide, lead octanoate, lead peroxide, lead sulphate, and tri lead-bicarbonate – dihydroxide;

4/ “Products that use lead in paint as an input” includes children’s toys, indoor or outdoor playground equipment, children's books, art materials, home furnishing materials and other products that use lead in paint as an input;

5/ “Certificate of conformity assessment” means a certificate issued to approve a paint product that meets a minimum limit set in this Regulation;

6/ “Label” means a written ,printed or graphic matter on or attached to the immediate container of a paint and the outside container or wrapper of the immediate containers in Amharic or English language about the total lead concentration;

7/ “Total lead concentration” means a weight percentage of the total non-volatile portion of the product or weight of the dried paint film;

8/ “Competent authority” means any governmental body which has mandate to control lead in paint according with this regulation and other laws;

9/ “Ministry and Minister” means the Ministry and Minister of Environment, Forest and Climate Change, respectively;

10/ “person” means any natural person or juridical organ;

11/ “Any expression in the masculine gender includes the feminine.

https://chilot.me



**፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ ማንኛውንም የሊድ ቀለም እና ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶችን በሚያመርት፣ ወደ ሀገር ውስጥ በሚያስገባ፣ ወደ ውጭ ሀገር በሚልክ፣ በጅምላ በሚሸጥ፣ በሚያከፋፍል እና በሚቸረችር ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>በቀለም የሊድ መጠን</u>

**፬.<u>በቀለም ውስጥ ሊኖር የሚገባው የሊድ መጠን</u>**

፩/ በሊድ ቀለም ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት በሚጠቀሙ ምርቶች ውስጥ የሊድ መጠኑ ከ፺ ፓርትስ ፐር ሚሊየን መብለጥ የለበትም።

፪/ ማንኛውም ሰው አጠቃላይ የሊድ መጠኑ ከፓርትስ ፐር ሚሊየን በላይ የሆነ ሊድ ቀለምን ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት በሚጠቀሙ ምርቶች ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ወደ ውጭ ሀገር መላክ፣ በጅምላ መሸጥ፣ ማከፋፈል ወይም መሸጥ አይችልም።

፫/ ሚኒስቴሩ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር በሊድ ቀለም ውስጥ ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት በሚጠቀሙ ምርቶች ላይ ሊኖር የሚገባው አጠቃላይ የሊድ መጠንን መከለስና በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ማስወሰን ይችላል።

**፭.<u>ስለ መለያ ምልክት</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው ሊድ ቀለም ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች የሚያመርት፤ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባ፣ ወደ ውጭ ሀገር የሚልክ፣ በጅምላ የሚሸጥ፣ የሚቸረችር ወይም የሚያከፋፍል መያዣያው ላይ አጠቃላይ የሊድ መጠን በግልጽ በሚታይ መልኩ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ የመለያ ምልክት መለጠፍ ወይም መለያ ምልክት መኖሩን ማረጋገጥ አለበት።

፪/ የመለያ ምልክት ያልተደረገበት ሊድ ቀለም ወይም ሊድ ያለውን ቀለም በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶችን ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ በጅምላ መሸጥ፣ ማከፋፈል፣ መቸርቸር ወይም ወደ ውጭ ሀገር መላክ የተከለከለ ነው።

**፮.<u>የተስማሚነት ምዘና የምስክር ወረቀት</u>**

፩/ ሊድ ቀለምን ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብአትነት የሚጠቀም ምርት በማምረት ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አግባብነት ካለው መስሪያ ቤት የተስማሚነት ምዘና የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት።

**3. <u>Scope of Application</u>**

This Regulation shall apply to any person who engages in manufacturing, importing, exporting, wholesaling, distributing and retailing of paints and products that use lead in paint as an input.

## <u>SECTION TWO</u>

## <u>CONCENTRATION OF LEAD IN PAINT</u>

**4. <u>Concentration of Lead in Paint</u>**

1/ The total concentration of leads in paint or any paint product that uses lead in paint as an input shall not be above 90 parts per million.

2/ Any person shall not manufacture, import, export, wholesale, distribute or retail paints with a total lead concentration higher than 90 parts per million.

3/ The Ministry in consultation with appropriate organs may review the concentration of leads in paint or any paint product that uses lead in paint as an input and cause decision by the Standards Agency.

**5. <u>Labeling</u>**

1/ Any person who manufactures, imports, exports, wholesales, distributes or retails any lead in paints or products that use lead in paint as an input shall label or ensure that the package of the lead in paint or the product has been labeled in Amharic or in English language in a conspicuous manner about the total concentration of lead.

2/ It is prohibited to manufacture, import, export, wholesale, distribute or retail any lead in paints or products that use lead in paint as an input without affixing a label.

**6. <u>Certificate of Conformity Assessment</u>**

1/ Any person who seeks to engage in the manufacturing of lead in paint or products that use lead in paint shall obtain a certificate of conformity assessment from the relevant government organ.

https://chilot.me


፪/ ሊድ ቀለምን ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አግባብነት ካለው መስሪያ ቤት ዘንድ ናሙና አቅርቦ በማስመርመር የተስማሚነት ምዘና የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት።

**ክፍል ሶስት**

**የሊድ ቀለም አወጋገድና የጥንቃቄ እርምጃዎች**

**፯.የሊድ ቀለም አወጋገድ**

፩/ የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው ሊድ ቀለሞች ወይም ሊድ ያለበትን ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች፤ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ሊድ ቀለሞች ወይም ሊድ ያለበትን ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች ይህ ደንብ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው ዘዴ መወገድ አለባቸው፡፡

፪/ አካባቢያዊ ተቀባይነት ያለው የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ መርሆችና ዘዴዎች እንደአግባብነቱ በሊድ ቀለም ወይም ሊድ ያለበትን ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች አወጋገድ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

**፰. የጥንቃቄ እርምጃዎች**

፩/ ሊድ ቀለምን ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች አያያዝ ወይም አመራረት ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው የሠራተኞችን ደኅንነትና ጤንነት ለመጠበቅ አስፈላጊና በቂ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል።

፪/ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ላይ የተደነገገው የሙያ ደኅንነት፣ ጤንነትና የሥራ አካባቢ መስፈርቶች ሊድ ቀለም ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶች አያያዝ ወይም አመራረት ሥራ ላይ በተሰማራ ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፫/ ማንኛውም ሰው ወይም የሕንጻ ባለቤት የሕንጻ ግንባታዎችን ከማፍረሱ በፊት ሕንጻው የተቀባበት አጠቃላይ የሊድ ቀለም መጠኑ በዚህ ደንብ ከተቀመጠው የሊድ መጠን በላይ መሆን አለመሆኑን ማስመርመር እና የሊድ ቀለም መጠኑ በዚህ ደንብ ከተመለከተው መጠን በላይ መሆኑ ሲረጋገጥ ግንባታው በሚፈርስበት ወቅት ተገቢ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ ወይም የጥንቃቄ እርምጃዎች መወሰዳቸውን መረጋገጥ አለበት።

2/ Any person who wants to import or exports lead in paints or products that use lead in paint as an input shall submit the sample of the product to the relevant government organ and obtain a certificate of conformity assessment.

**SECTION THREE**

**DISPOSAL OF LEAD IN PAINT AND SAFETY MEASURES**

**7.DISPOSAL OF LEAD IN PAINT**

1/ Obsolete paints or products that use lead in paint as an input, or paint and products that use lead in paint as an input which are manufactured or imported after the entry in to force of this Regulation shall be disposed in an environmentally sound manner.

2/ Principles and techniques of environmentally sound management and disposal of hazardous wastes, as appropriate, shall also be applicable to the disposal of lead in paint and products that use lead in paint as an input.

**8. Safety measures**

1/ Any person engaged in the management or production of paints or products that use lead in paint as an input shall take necessary and adequate measure to safeguard the health and safety of the workers.

2/ The occupational health and safety requirements provided under the Labor Proclamation shall be applicable to person engaged in the management or production of lead in paints or products that uses lead in paint as an input.

3/ Any person or owner of building shall have obligation to cause examination of the concentration of lead in paint before demolition of building; and if the lead concentration in the paints of the building is found above the standard provided in this Regulation, adequate safety measure shall be taken or ensure that adequate safety measures are put in place.

https://chilot.me



፬/ የሊድ ቀለም ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት በሚጠቀሙ ምርቶች አያያዝ ላይ ወይም አመራረት ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ሚኒስቴሩ የሚያወጣውን መመሪያ የመከተል እና፡-

ሀ) ስለጥንቃቄ እርምጃዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት የመስጠት እና

ለ) በሕፃናት ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ለመከላከል እና ተጋላጭነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎችን የመውሰድ ኃላፊነት አለበት።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፱.አስተዳደራዊ እርምጃዎች

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ ከተመለከተው መጠን በላይ የሆነን ሊድ ቀለም ወይም ሊድ ያለው ቀለምን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ምርቶችን ያመረተ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባ ወይም ወደገበያ ያሠራጨ እንደሆነ አግባብነት ያለው አካል፡-

ሀ) ምርቱ በአገር ውስጥ በአገልግሎት ላይ እንዳይውል የማገድ፤

ለ) የባለፈቃዱ የንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

፪/ አግባብነት ያለው አካል በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወሰደውን አስተዳዳራዊ እርምጃ ለሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ አካል በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

### ፲. የመተባበር ግዴታ

የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል የፌደራልና የክልል መንግሥት አካላት እንዲሁም ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት።

### ፲፩. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩/ ይህ ደንብ ከመጽደቁ በፊት የሊድ ቀለም በማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት፣ ወደ ውጭ ሀገር በመላክ፣ በጅምላ በመሸጥ፣ በማከፋፈልና በመቸርቸር ሥራ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ይህ ደንብ በሥራ ላይ በዋለ በአንድ ዓመት ውስጥ የቀለም ሊድ መጠኑን ፺

4/ Any person engaged in the management or production of lead in paint or product that uses lead in paint as an input shall have the responsibility to follow the directive issued by the Ministry and to:

a) Undertake awareness creation trainings about safety measures and

b) Take measures that reduce exposure of children and prevent harm against children.

## SECTION FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 9. Administrative Measures

1/ When any licensed person produces, imports, wholesales, distributes or retails lead in paint or product that uses lead in paint as an input which has concentration above the standard provided in this Regulation, competent authority may take the following administrative measures:

a) Ban the product from domestic transaction;

b) Suspend or cancel the business license of the licensee.

2/ The competent authority shall notify to the relevant licensing body the measure taken under sub-article (1) of this Article.

### 10. Duty to co-operate

In order to implement the provisions of this Regulation the Federal and Regional government organs as well as any person shall have the duty to co-operate with the Ministry.

### 11.Transitional Provisions

1/ Any person who started to manufacture, import, export, wholesale, distribute or retail lead in paint before the entry into force of this Regulation shall bring down the total concentration of lead in paint below 90

https://chilot.me



ፓርትስ ፐር ሚሊየን ወይም ከዚያ በታች ማውረድ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የመሸጋገሪያ ጊዜ የሊድ ቀለምን በግብዓትነት በሚጠቀሙ ምርቶች ንግድ ሥራ ላይ በተሰማራ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆንበታል፡፡

## ፲፪. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ይህንን ደንብ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሚኒስቴሩ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲፫ .ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ኃዳር ፬ ቀን ፪ሺ፲፩

አብይ አህመድ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

Parts per million withi one year or below that after the entry into force of this Regulation.

2/ The transitory period provided under sub-article (1) of this Article shall apply to any person who is engaged in the business of products that use lead in paint as an input.

## 12. Power to issue Directives

The Ministry may issue directives necessary for the implementation of this Regulation.

## 13. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazzete.

**Done at Addis Ababa , 13th Day of November of 2018.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://chilot.me



.

<u>Corrigendum No.13/2010</u>

Article 12(1) of Ethiopian Geospatial Information Agency Re-Establish the Proclamation No. 1079/2018 Amharic version which read as “The Agency … complete and accurate books of account” is hereby corrected and shall be read as “The Agency shall keep complete and accurate books of account”.

Artic
Re-E
versi
accur
read
book